# ውጋጆችን በድጋሚ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ስናደርግ ሁላችንም አሸናፊዎች እንሆናለን

**ምንም አይነት ማሸጊያ ወይም ጋዜጣ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል በሚያስቀምጡበት ጊዜ ሁሉ፣ ይህ ተግባርዎ የአንድ ትልቅ ነገር መጀመሪያ እንደሆነ ያስታውሱ።**

አሮጌው የጠርሙስ ክዳን ለመኪና አካላት ወደ አዲስ የብረት ሉህ ሊቀየር ይችላል። ለምሳሌ፣ አንድ ባዶ የማጠቢያ ሳሙና ማስቀመጫ አዲስ የፒዛ ካርቶን ሊወጣው ይችላል። የትላንትናው ጋዜጣ የነገ ዋና ርዕስ ተደርጎ ሊወጣ ይችላል። ተፈጥሮ የለገሰችንን ጥሬ እቃዎች እንደገና ጥቅም ላይ ስናውላቸው ከፍተኛ መጠን ያለው ሀይል መቆጠብ እንችላለን። ይህንን በማድረግም ለመኖሪያ ምቹ የሆነ የተሻለ ዓለም ለመፍጠር የበኩላችን አስተዋጽኦ እናበረክታለን።

**መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል**

የምግብ ትራፊt እንደ ባዮጋዝ እና ባዮ ማዳበሪያነት መልሶ ጥቅም ላይ ይውላሉ እንዲሁም ቀሪ ቆሻሻዎች ኤሌክትሪክ እና ሙቀት ይቀየራሉ። ሁሉም ዓይነት የተሰበሰቡ ውጋጅ ማሸጊያዎች እና ጋዜጦች አዲስ ማሸጊያዎች ወይም አዲስ ምርቶች እንዲሆኑ ለማድረግ እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። ለምሳሌ፣ የፕላስቲክ ማሸጊያዎች ብዙውን ጊዜ ፕላስቲክ የመያዣ ቦርሳዎችና እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መያዣዎችን ለመስራት እንደ ዋና ግብዓት ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። የጠርሙስ እና የወረቀት ማሸጊያዎች አብዛኛውን ጊዜ ተጨማሪ ማሸጊያዎች ሊወጣቸው ይችላል። የብረታ ብረት ማሸጊያ የጎማ ቸርኬ ሊሆን ይችላል እንዲሁ አሮጌ ጋዜጣዎች ወደ የወጥ ቤት ወረቀት ወይም አዲስ የጋዜጣ እትም ሊቀየር ይችላል።

**የቆሻሻ ማስወገጃ ክፍሎች እና እንደገና ጥቅም ላይ የማዋያ ጣቢያዎች**

የምግብ ቆሻሻ እና ቀሪ ቆሻሻ እርስዎ በሚኖሩበት ቦታ በልዩ የቆሻሻ መጣያዎች ለምሳሌ በቆሻሻ ማስወገጃ ክፍሎች ውስጥ መጠራቀም አለባቸው። በሚኖሩበት ቦታ ማሸጊያዎችን ወይም ጋዜጦችን የሚያጠራቅሙበት ቦታ ከሌለ ይልቁንስ ሰው አልባ ወደሆነ የመልሶ መጠቀሚያ ጣቢያ ይውሰዷቸው፣ ይህም ጣቢያ። ለእያንዳንዱ ዓይነት ማሸጊያ እቃዎች: ፕላስቲክ፣ ወረቀት፣ ብረት እና መስታወት እና ብዙ ጊዜ ጋዜጦችም ያሉበት ማስቀመጫ አለው።በሚኖሩበት ቦታ የቆሻሻ መጣያዎች ውስጥ የማይገቡ ትላልቅ ማሸጊያዎች በድጋሚ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጣቢያዎች ወይም በድጋሚ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ማእከላት ውስጥ ሊጣሉ ይችላሉ።

**ተጨማሪ መረጃ**

**www.sopor.nu** ላይ በአቅራቢያዎ ያለውን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋያ ቦታ ሊያገኙና መቼ ባዶ እንደሚሆንና እንደሚጸዳ ሊያውቁ ይችላሉ። በተጨማሪም እንዴት መለየት እንደሚችሉ የሚያሳይ መመሪያ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ስለማዋል የሚያሳዩ ቪዲዮዎችን፣ ጠቃሚ ምክሮች እና ከምንጩ ላይ ስለመደርደር ምክሮች እዚህ ይገኛሉ።.

ስለ ቆሻሻ እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋልን በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት የከተማ አስተዳደርዎን ማነጋገር ይችላሉ። እንዲሁም ስለ ትልቅ ቆሻሻ፣ ብስባሽ፣ የኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክ   የተጣሉ ዕቃዎች እና ሌሎች ቆሻሻዎች ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ።

amaq ANEBY MILJÖ & VATTEN AB · EKSJÖ ENERGI · NÄSSJÖ AFFÄRSVERK · sopor.nu Sveriges avfallsportal

# በመልክ በመልኩ መለየት

**የተቻለውን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ውጋጅ እንደገና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የእርስዎ እገዛ ያስፈልገናል።**

- የተለያዩ ቆሻሻዎችን አትቀላቅሉ።
- የምግብ ቆሻሻዎች ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀው ልዩ ቦርሳ ውስጥ ብቻ መቀመጥ አለባቸው።
- የተረፈ ቆሻሻ በጥብቅ በታሰረ ቦርሳ ውስጥ መቀመጥ አለበት።
- ማሸጊያዎቹ ሙሉ በሙሉ ባዶ መደረግና ደረቅ መሆን ይኖርባቸዋል። ያለዎት ከአንድ በላይ በሆነ ግብዓት የተሰራ ማሸጊያ ከሆነ ይበልጥ ክብደት ያለውን በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርብዎታል።

**የምግብ ትርፊ**

✓ የፍራፍሬ እና የአትክልት ቅሪቶች፣ የሻይ ከረጢቶች፣ የቡና አተላ፣ የእንቁላል ቅርፊቶች፣ የስጋ አጥንት እና የመሳሰሉት። ትንሽ የወጥ ቤት ወረቀት እንዲሁ ጥሩ ነው።

✗ ፕላስቲክ፣ ማናፈጫ፣ ሲጋራ፣ አበባ እና ሻማ የምግብ ቆሻሻ አይደሉም።

**የፕላስቲክ ማሸጊያ**

✓ ጠርሙሶች፣ ቆርቆሮዎች፣ የፕላስቲክ መያዣዎች፣ ድጋሚ የሚሞሉ ማሸጊያዎች፣ የፕላስቲክ ቱቦዎች፣ ፓኬቶችና ፖሊስትሪን። ማንኛውንም ዓይነት ቆርኪዎችንና ክዳኖችን ያስወግዱ። የተለያዩ የፕላስቲክ ማሸጊያዎችዎን ለእያንዳንዱ በተዘጋጀው መያዣ በማስገባት ቦርሳዎን ባዶ ያድርጉ። ይህ በኋለኛው እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ጊዜ ሂደቱን ቀላል ያደርገዋል።

✗ ከማሸጊያዎች በስተቀር ፕላስቲክ ምርቶች፣ ከባድ ወይም የቤት ውስጥ ውጋጅ ተደርገው በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፣ የቤት ውስጥ መገልገያዎች እና አሻንጉሊቶች። በመያዣ የተገዙ ጠርሙሶችን ወደ ሱቆቹ በመመለስ ገንዘቡን ማስመለስም ያስፈልጋል።

**የብረት ማሸጊያዎች**

✓ የቆርቆሮ ጣሳዎች፣ ባዶ የመርጨ ቆርቆሮዎች፣ ቱቦዎች፣ ቆርኪዎች፣ ክዳኖች እና ባዶ የቀለም ቆርቆሮዎች። ጣሳዎቹ ላይ ያለውን ስል ጫፍ ይጠፉ።

✗ ቀለም ወይም ማጣበቂያ ያላቸው ጣሳዎች አደገኛ ውጋጅ ተደርገው በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርባቸዋል። ቁርጥራጭ ብረታ ብረቶች፣ የቧንቧ ክፍሎች፣ ምግብ መጥበሻዎች፣ እና ሌሎች ምርቶች የቤት ውስጥ ውጋጆች ተደርገው በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርባቸዋል። በመያዣ የተገዙ ጣሳዎችን ወደ ሱቆቹ በመመለስ ገንዘቡን ማስመለስም ያስፈልጋል።

**የወረቀት ማሸጊያዎች**

✓ የፓስታ ማሸጊያ፣ የወተትና የጭማቂ ካርቶኖች፣ የወረቀት መያዣዎች፣ የጫማ ሳጥኖች፣ የመጸዳጃ ቤት ወረቀት መያዣ ቱቦዎች እና የካርቶን ሳጥኖች። ይዘርጓቸውና ለሁለት ይጠፏቸው። ቦታ ለመቆጠብ ትንንሾቹን ማሸጊያዎች በትልልቅ ማሸጊያዎች ውስጥ ያስገቡ።

✗ ፖስታዎች እንደ ቤት ውስጥ ውጋጅ ወይም ለፍግነት የሚያገለግሉ ውጋጅ ተደርገው በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርባቸዋል። ጋዜጦች፣ የማስታወቂያ በራሪ ወረቀቶች እና ተመሳሳይ ነገሮች ለጋዜጦች በተዘጋጀው ማስቀመጫ ውስጥ መደረግ ይኖርባቸዋል።

**ጋዜጦች**

✓ እለታዊ እና ሳምንታዊ ጋዜጦች፣ መጽሄቶች፣ ካታሎጎች፣ የማስታወቂያ በራሪ ወረቀቶች፣ ማስታወሻ መጻፊያ ደብተሮች፣ የመጻፊያ/የስዕል መሳያ ወረቀቶች። የፕላስቲክ መጠቅለያዎችና የማስታወቂያ ተለጣፊዎችን ያስወግዱ።

✗ ፖስታዎችና የተጠረዙ መጽሐፍት የቤት ውስጥ ውጋጅ ወይም ለፍግነት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ተደርገው በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርባቸዋል። የወረቀት ቦርሳዎች፣ ካርቶኖች እና ተመሳሳይ ነገሮች ለወረቀት ማሸጊያነት ተብለው በተዘጋጁ መያዣዎች ውስጥ መቀመጥ ይኖርባቸዋል።

**ቀለም የሌላቸው የብርጭቆ እሽጎች**

✓ ቀለም ያላቸው ወይም ቀለም አልባ ጠርሙሶች እና ብልቃጦች። ቆርኪዎች፣ ክዳኖችና ቡሾች በተገቢው መንገድ በመልክ በመልክ መለየት ይኖርባቸዋል። ባለቀለም እና ቀለም አልባ የጠርሙስ ማሸጊያዎችን በመልክ በመልኩ ለይተው በትክክለኛው መያዣ ያስቀምጡ።

✗ በመያዣ የተገዙ ጠርሙሶችን ወደ ሱቆቹ በመመለስ ገንዘቡን ማስመለስም ያስፈልጋል። ማሸጊያ የሌላቸው የሸክላ እቃዎች፣ ሴራሚኮች እና ሌሎች ምርቶች የቤት ውስጥ ውጋጅ ተደርገው በመልክ በመልኩ መለየት ይኖርባቸዋል። አምፖሎችና መብራቶች በአካባቢው ወደሚገኙት እንደገና ጥቅም ላይ የሚያውሉ ማእከሎች መወሰድ ይኖርባቸዋል።

**ተረፈ ምርት**

✓ የሽንት ጨርቆች፣ ኤንቨሎፖች፣ የእቃ ማጠቢያዎች፣ ማናፈጫ፣ የጥርስ ብሩሾች እና ፀጉር ከጸጉር ብሩሽ።

✗ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ምንም ነገር በተለመደው ቆሻሻ መጣያ ውስጥ መቀመጥ የለበትም! አደገኛ ቆሻሻ እና የኤሌክትሪክ ቆሻሻ ከመደበኛ ቆሻሻዎ መራቅ አለባቸው; እነዚህ ይልቅስ ወደ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማእከል መወሰድ አለባቸው።

**እናመሰግናለን**

amaq ANEBY MILJÖ & VATTEN AB
EKSJÖ ENERGI
NÄSSJÖ AFFÄRSVERK
sopor.nu Sveriges avfallsportal